የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት
Road Safety & Insurance Fund Service

# የተሽከሪካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለመግጠም እና ስለ ማስተዳደር የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር …. /2017.

ሐምሌ/ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**መግቢያ**

የዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት እና የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች እንደሚያሳዩት መካከለኛ እና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸዉ የዓለማችን ሀገራት ከ50% በላይ የሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎች ክስተት ዋነኛ መንስኤዉ ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በሀገራችንም የመንገድ ትራፊክ አደጋ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለዚህም አደጋ ዋና መንስኤ ከፍጥነት ወሰን በላይ ማሽከርከር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም በተሽከሪካሪዎች ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ በመግጠም የተሽከሪካሪዎችን ፍጥነት በመገደብ አደጋዉን መቀነስ ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡

በመሆኑም የትራንፖርትና ሎጅስኪስ ሚ/ር የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር..../2017 አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 5 በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ /ማሻሻያ/ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የተሽከሪካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለመግጠም እና ስለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር( ማሻሻያ) ..... /2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፡

1. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር..../2016 ነው፡፡
2. በደንቡ አንቀጽ 2 ሥር የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
3. **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
4. **"አገልግሎት"** ማለት የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ማለት ነዉ፡፡
5. **"ቢሮ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ወይም የመንገድ ደህንነትን ወይም የመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ሥራን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠዉ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ነዉ፡፡
6. **"የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ"** ማለት በተሽከሪካሪ ላይ የሚገጠም የተቀናጀ የተሽከሪካሪ ፍጥነት መቆጣጠሪያ መሳሪያ ከዓለም አቀፍ ሥርዓት አቅጣጫ (GPS) ጋር የተጣመረ ሆኖ እንደተሽከሪካሪዉ ሁኔታ ወደ ሞተሩ የሚገባዉን ነዳጅ ወይም አየር በመቀነስ እንዲሁም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎችን ታሳቢ ያደረገ የተሽከሪካሪ ፍጥነት በህግ ከተደነገገው በላይ እንዳይፈጥን የሚቆጣጠር መሳሪያ ነዉ፡፡
7. **" የሚመለከተዉ አካል"** ማለት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ በተሽከሪካሪዎች ላይ እንዲገጠም የመፍቀድ ስልጣን ወይም ዉክልና ያለዉ አካል ነዉ፡፡
8. **"የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አስመጪ እና ገጣሚ ድርጅት"** ማለት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን ከሚያመርተዉ ድርጅት ዉክልና ያለው፣ከሚመለከተው አካል የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የማስገባት፣ የመግጠም እና የማስተዳደር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠዉ ድርጅት ማለት ነዉ፡፡
9. **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
10. **"የመንግስት ከፍተኛ የሥራ ሀላፊዎች"** ማለት ሚኒስቴሮች፤ሚኒስቴር ደኤታዎች፤የተቋም ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፤ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፤ የክልል ፕሬዝዳንቶች ፤ ምክትል ፕሬዝዳንቶች እና በዚህ ደረጃ የሚገኙ አመራሮች ናቸዉ፡፡

11. **" ከባድ ማሽነሪዎች"** ማለት በተለያዩ ግንባታዎች ላይ የሚሳተፉ የኮንስትራክሽን ተሽከሪካሪዎች ሲሆኑ (የዉሃ ጉድጓድ መቆፈሪያ ማሽኖች እና ክሬኖችን) ያካትታል፡፡
12. **" የድንገተኛ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች" ማለት** አምቡላንሶች፤ የእሳት አደጋ ተሽከሪካሪዎች፤ የጸጥታ እና ደህንነት ተሽከሪካሪዎች ናቸው፡፡
13. **" ሰዉ"** ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በህግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ነዉ፡፡
14. ማንኛዉም በወንድ ጾታ የተገለጸዉ ሴትንም ያካትታል፡፡

**3. ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተሽከሪካሪዎች ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጠም በማድረግ የተሽከሪካሪ ፍጥነት የሚያስከትለዉን የመንገድ ትራፊክ ግጭት መጠንና ጉዳት መከላከልና መቀነስ ነዉ፡፡

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ከሚፈቀድላቸው ተሽከርካሪዎች በስተቀር በሁሉም የኢትዮጵያ መንገዶች ላይ በሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች አገልግሎቱ በሚያወጣዉ የአፈጻጸም ቅደም ተከተል መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

**የተሽከሪካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እና የሚገጠምላቸዉ ተሽከሪካሪዎች ዓይነት፡**

**5. የተሽከሪካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ**

1. በተሽከሪካሪ ላይ የሚገጠም የተቀናጀ የተሽከሪካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ከዓለም አቀፍ ሥርዓት አቅጣጫ (GPS) ጋር የተጣመረ ሆኖ በስታንዳርዱ የተቀመጡ መለኪያዎችን ያሟላ ሆኖ ተሽከሪካሪው በህግ ከተደነገገው በላይ እንዳይፈጥን የሚገድብ መሳሪያ መሆን አለበት፡፡
2. በተሽከሪካሪ የሚገጠመዉ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጣቸዉ የንግድ ተቋማት ብቻ የተገዛ እና የሚገጠም ሲሆን ለዚህም መሳሪያዉ የአምራች መለያ ቁጥር እና ኪውአር ኮድ(QR code) ያለዉ መሆን አለበት፤
3. መሳሪያዉ ከኔትወርክ ዉጪ (Offline) ሆኖ የሚሰራ፤ ኔትወርክ ሲያገኝ መረጃዎቹን ወዲያዉኑ የሚያስተላልፍ እና ተጨማሪ አገልግሎቶች እንዲሰጥ ሲታከልበት ከመረጃ ቋት ( Data Base) ከያዘዉ ኮምፒዩተር ጋር በመረጃ መረብ ተገናኝቶ የሚናበብና መረጃ የሚያስተላልፍ መሆን አለበት፤
4. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ ተሽከሪካሪዉ ከተወሰነለት ፍጥነት በታች ፍጥነቱን እንዲቀንስ በህግ በሚገደድበት ሁኔታዎች ሲኖር ተሽከሪካሪዉ ከፈጠነ በድምጽ ወይም በምልክት ፍጥነቱን እንዲቀንስ ለአሽከሪካሪዉ የሚያስጠነቅቅ እና ወደ መረጃ ማዕከሉ መረጃ ማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፤
5. በኤለክትሪክ ወይም በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ለሚሰሩ ተሽከሪካሪዎች እንደአስፈላጊነቱ ኤለክትሪክ ሀይሉን በመቀነስ የተሽከሪካሪ ፍጥነት እንዲቀንስ የሚያደርግ መሳሪያ መሆን አለበት፤
6. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ በሀገር ዉስጥ የኔትወርክ አገልግሎት የሚሰጡ የቴሌኮም ድርጅቶች የሚሰራ ሆኖ የአመታዊ ጥቅል አገልግሎት ያለዉ መሆን አለበት፡፡

**6. የተሽከሪካሪ የፍጥነት ወሰን መጠን**

1. በተሽከሪካሪዎች ላይ የሚገጠመዉ የፍጥነት መገደቢያ ጣሪያ የፍጥነት ወሰን ህጉ በሚደነግገዉ ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን ጣሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገዉ ቢኖርም አሽከሪካሪዉ በትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ መሠረት ፍጥነቱን ከተፈቀደለት የፍጥነት ወሰን በታች ማሽከርከር የሚገባዉ ሁኔታ ሲኖር ፍጥነቱን ቀንሶ ማሽከርከር ይገባዋል፡፡

**7. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስታንዳርድ ዝግጅት፡**

የተሽከሪካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስታንዳርድ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት(IES) ባወጣዉ የስታንዳርድ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**8. ልዩ ሁኔታ**

በአንቀጽ 4 ላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የድንገተኛ አገልግሎት ተሽከሪካሪዎች፤ የመንግስት ከፍተኛ የሥራ ሀላፊዎች የሚጠቀሟቸዉ ተሽከሪካሪዎች፤የዲፕሎማት ተሽከሪካሪዎች፤ የፋይናንስ ተቋማት ለገንዘብ ዝዉዉር የሚጠቀሟቸዉ ተሽከሪካሪዎች፤ ከባድ ማሽነሪዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

# ክፍል ሦስት

# የተለያዩ አካላት ኃላፊነት

**9. የሚኒስቴሩ ኃላፊነት፡**

1. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ መመሪያን በማጽደቅ ወደ ስራ እንዲገባ ያደርጋል፡፡
2. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ አተገባበር ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**10. የአገልግሎቱ ኃላፊነት፡**

1. የፍጥነት መገደቢያ መሣሪያ ለሚያቀርበዉና ለሚገጥመዉ አካል በወጣዉ መስፈርት መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል ወይም የሚመለከተው አካል ፍቃድ እንዲሰጥ ውክልና ይሰጣል፡፡
2. ወጥነት ያለዉ የፊሊት ማኔጅመንት ሶፍትወር (Software) በማልማት ለአቅራቢና ገጣሚ ድርጅቶች ይሰጣል፡፡
3. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አተገባበር በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ የሚያደርግ ኢንተግረትድ ሶፍትወር ( Integrated Soft Ware) እና የአተገባበር ሂደትን ከወረቀት ሥራ ማላቀቅ የሚችል መተግበሪያ ያበለጽጋል፡፡
4. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ መተግበሪያዉ ላይ ሱፐር አድሚኑን በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡
5. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸዉ ተሽከሪካሪዎችን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ በህጉ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፡፡
6. ድንገተኛ የተሽከሪካሪ ምርመራ በማድረግ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ ስለመገጠሙ፤ በትክክል ስለመስራቱ እና በአግባቡ ስለመታሸጉ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይህንን ባላሟሉ ተሽከሪካሪዎች ላይ እርምጃ ይወስዳል፡፡

7. በዚህ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ከተፈቀደዉ ተሽከሪካሪ በስተቀር የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ መግጠም ያለበት ማንኛዉም ተሽከሪካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ያልተገጠመለት ከሆነ ዓመታዊ የተሽከሪካሪ ማረጋገጫ ሰርቲፍኬት(ቦሎ) እንዳያገኝ መደረጉን ይከታተላል፡፡
8. የተሽከሪካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ገጣሚ ድርጅቶች በየዓመቱ ለቴሌኮም ኩባንያዎች የሚከፍሉትን የአገልግሎት ክፊያ እየፈጸሙ እድሳት ማድረጋቸዉን፤ እንዲሁም ተሽከሪካሪዉ ለ3ኛ ወገን ሲተላለፍ በዉስጡ ያለዉ ማሽን ለማሽን ሲም ካርድ እና በዉስጡ ያለዉ ዓመታዊ ጥቅል አብሮ መተላለፉን በክትትልና በቁጥጥር ያረጋግጣል፡፡
9. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የሚያቀርበዉና የሚገጥመዉ አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ስለመኖሩና ፈቃዱ ስለመታደሱ ያረጋግጣል፡፡
10. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን እና የሚገጠምላቸዉን ተሽከሪካሪዎች ዓይነት ቅደም ተከተል የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ወይም ማኑዋል በማዘጋጀት ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
11. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ለገጠመ ተሽከሪካሪ ፎርጅድ እና መሰል ማጭበርበርን ለመከላከል በቴክኖሎጂ የተደገፈ ( ባር ኮድ/ማይክሮ ቺፒስ ) ልዩ ምልክት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡
12. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር የተሽከሪካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዎች የጥራት ደረጃ እና የቴክኒክ ስፔስፊኬሽን እንዲወጣ ያደርጋል፤ የዕድሳት ጊዜዉንም ይወስናል፡፡
13. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የገጠሙ ተሽከሪካሪዎችን ለመከታተል እንዲያስችል የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት መረጃዎችን ይይዛል፡፡
14. ስለ መመሪያዉ አተገባበር ለተለያዩ አካላት ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡
15. የመመሪያዉን ተግባራዊነት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ያረጋግጣል፤ መመሪያዉን ተላልፈዉ በሚገኙ አካላት ላይ ተገቢዉን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

**11. የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ሀላፊነት**

1. ከአገልግሎቱ በሚሰጠው ውክልና መሰረት ለፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ገጣሚ እና አቅራቢ ድርጅት በመመሪያዉና በማንዋሉ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ያድሳል፤ይሰርዛል፡፡
2. በተሽከሪካሪዉ ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እና ጂ.ፒ.ኤስ በትክክል ስለመገጠሙ የማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፤
3. ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ለፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አስመጪና ገጣሚ ድርጅቶች፤ በደረቅ ወደብ ለሚገኙ የተሽከሪካሪ ቴክኒሽያኖች እና ለሚመለከታቸዉ አካላት ስለሶፍትዌሩ ሥልጠና ይሰጣል፡፡
4. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸዉን እንዲሁም በሀገር ዉስጥ ታርጋ አዉጥተዉ የሚንቀሳቀሱ ተሽከሪካሪዎች መረጃ ወደ መተግበሪያዉ ቋት እንዲገባ ያደርጋል፡፡
5. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጥም ግዴታ ያለበት ተሽከሪካሪ መሳሪያዉን ያልገጠመ እንደሆነ ዓመታዊ የተሽከሪካሪ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡
6. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የገጠሙ ተሽከሪካሪዎች አደጋን ከመከላከል አንጻር ያላቸዉን ሚና ይከታተላል፡፡
7. የተሽከሪካሪ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለመግጠም የወጣውን መመሪያ ለማስፈጸም የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ያከናዉናሉ፤ በየጊዜዉ ለአገልግሎቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡
8. በክትትልና ቁጥጥር ያገኙትን መረጃ ለአገልግሎቱ ያስተላልፋሉ፡፡
9. የተሽከርካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ላላስገጠሙ ተሽከርካሪዎች ሠሌዳ ወይም የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ቦሎ/ መስጠት የለበትም፡፡

**12. የተሽከሪካሪ ባለንብረት ሀላፊነት፡**

1. ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለንብረት በተሽከርካሪው ላይ የሚገጥመው የተሽከርካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ በተሽከርካሪ ላይ እንዲገጥም እና እንዲያስተዳድር ህጋዊ ፈቃድ ከተሰጠው ድርጅት ብቻ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛዉም የተሽከሪካሪ ባለንብረት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ እንዲገጠም በመመሪያዉ የተካተተዉን ተሽከሪካሪ መሳሪያዉን ሳይገጥም እንዲሽከረከር መፍቀድ የለበትም፡፡
3. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ትክክለኛዉን አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ፤ ብልሽት ሲገጥመዉ እና ከአሽከሪካሪዉ ሪፖርት ሲቀርብ እንዲስተካከል የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
4. የተሽከሪካሪ ባለንብረት ከገጣሚዉ አካል ጋር የሚደረጉ የዉል ስምምነቶች የማክበር እና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡
5. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ ሲበላሽ በ 10 (አስር) ቀናት ዉስጥ ገጣሚ ድርጅቱ ጋር በመቅረብ የማስተካከል ግዴታ አለበት፡፡

**13. የአሽከሪካሪዉ ሀላፊነት**

ማንኛዉም አሽከሪካሪ፡

1. አገልግሎቱ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጠምለት በመመሪያዉ ላይ የተካተተዉ ተሽከሪካሪ ዓይነት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን ሳይገጥምለት ማሽከርከር የለበትም፤
2. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ በተቀመጠዉ ስፔስፊኬሽን መሠረት የተገጠመና በታሰረዉ የፍጥነት ልክ (ጂ.ፒ.ኤስ) ጋር የተናበበ ወይም በአግባቡ የተገጠመ፤የታሸገ እና በትክክል የሚሰራ መሆኑን ሳያረጋግጥ ማሽከርከር የለበትም፡፡
3. በተሽከሪካሪዉ ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ መገጠሙን የሚያሳይ ሰርቲፊኬት መያዙን ወይም መኖሩን የማረጋገጥ፤ ከታሰረበት ፍጥነት በላይ መኪናዉ የሚሄድ ከሆነ በትክክል እየሰራ አለመሆኑን በመረዳት ወደ ገጣሚ ድርጅት በመሄድ ማስተካከያ የማስደረግ፤

**14. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ሀላፊነት**

1. የተሽከሪካሪዉን ፍጥነት ሲጠራጠር እና ድንገተኛ ቁጥጥር በማድረግ ተሽከሪካሪዉን በማስቆም የፍጥነት መገደቢያ በአግባቡ የተገጠመ፤ በአግባቡ የታሸገ እና በትክክል የሚሠራ መሆኑን ያረጋግጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ዲቫይሱ ( Device) ከራሱ ፕሪንተር ጋር በማገናኘት ወይም በዩኤስ ቢ ( USB) የፍጥነት መረጃ በመዉሰድ መመርመር ይችላል፡፡
2. በአደጋ ተሳትፎ ያላቸው ተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የሚመለከታቸው ተሽከሪካሪዎች ከሆኑ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለመገጠሙ እና በአግባቡ ስለመስራቱ የአደጋ ምርመራውን የሚያደርገው የትራፊክ ፖሊስ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የትራፊክ ተቆጣጣሪዉ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ ከተፈቀደዉ ፍጥነት በላይ የተገጠመ ወይም አግባብነት በሌለዉ ሁኔታ መታሸጉን ሲጠራጠር ከሚመለከተዉ ትራንስፖርት ቢሮ ትክክለኛነቱን አረጋግጦ እስኪመጣ የአሽከሪካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለ 2 ቀን ይዞ ይቆያል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አሽከሪካሪዉ በተቀመጠዉ ጊዜ ገደብ ዉስጥ ከሚመለከተዉ ትራንስፖርት ቢሮ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይዞ ካልመጣ የአሽከሪካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት የተያዘበትን ምክንያት በመግለጽ ፈቃዱን ያስተላልፋል፡፡

**15. የተሽከሪካሪ ምርመራ ተቋማት ሀላፊነት**

ማንኛዉም የተሽከሪካሪ ዓመታዊ ምርመራ እንዲያከናዉን ሥልጣን የተሰጠዉ አካል፡

1. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ በሚመለከተዉ ተሽከሪካሪ ላይ ስለመገጠሙ፤ በአግባቡ ስለመስራቱ እንዲሁም በአግባቡ ስለመታሸጉ ያረጋግጣል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ላላሟላ ተሽከርካሪ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስጠት የለበትም፡፡

16. **የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሀላፊነት**

1. ተሽከሪካሪዎች የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ በሚገቡበት ወቅት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ በተሽከሪካሪዉ ላይ ስለመገጠሙ የሚገልጽ ሰነድ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር "1" ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ያልገጠመ ተሽከሪካሪ የኢንሹራንስ ዉል ከመግባቱ በፊት መሳሪያዉን እንዲያስገጥም የማድረግ ሀላፊነት አለበት፡፡

**15. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አቅራቢ እና ገጣሚ ድርጅት ኃላፊነት**

ማንኛዉም የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የሚያቀርብ አካል፡

1. የሚያቀርበዉ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አገልግሎቱ የሚያወጣዉን መስፈርት እና ደረጃ የሚሟላት፤
2. ከሚመለከተዉ አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የማግኘት፤
3. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን የመግጠም፤ ጥገና እና እድሳት የማድረግ፤
4. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ ትክክለኛ መሆኑን፤ በተሽከሪካሪዉ ላይ በፍጥነት ወሰኑ ልክ በአግባቡ መገጠማቸዉን የማረጋገጥ እና ሪፖርት የመመዝገብ፤
5. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸዉ ተሽከሪካሪዎችን ብዛትና ዓይነት በተመለከተ በኤለክትሮኒክስ እና በማኑዋል መረጃዎችን በማደራጀት በየወሩ መጨረሻ ለአገልግሎቱ የማሳወቅ፤
6. ለፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ በቂ መለዋወጫ የማቅረብ፤
7. አገልግሎቱ በሚያወጣዉ መስፈርት መሰረት የጥገናና የእድሳት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለዉ የሥራ ቦታ እና ባለሙያ የማዘጋጀት፤
8. የዓለም አቀፍ ስርዓተ አቅጣጫ ( GPS) መቆጣጠሪያ ሰርቨርም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶች በሀገር ዉስጥ ሆኖ የሚያገለግል መሳሪያ የማቅረብ፤
9. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ አገልግሎቱ ባወጣዉ መስፈርት መሰረት ደረጃዉን የጠበቀ እና የተረጋገጠ መለያ (ብራንድ) መሳሪያ የማቅረብ፤
10. ድርጅቱ በማንኛዉም ጊዜ ከአገልግሎቱ፤ ከክልል እና ከተማ አስተዳደር ጥያቄ ሲቀርብ ፈጣን ምላሽ የመስጠት፤
11. አገልግሎቱ በየጊዜዉ የሚያወጣቸዉን የአሠራር ሥርዓቶች ተግባራዊ የማድረግ፤
12. የፍሊት ማኔጅመንት ሥርዓት በማደራጀት ከአገልግሎቱ ካለዉ የዳታቤዝ እንዲናበብ በማስቻል የተነቀለ፤ የተበላሸ እና አጠቃላይ የተገጠሙትን በመለየት በየወሩ ሪፖርት የማድረግ፤
13. ድርጅቱ በተሽከሪካሪዎች ላይ የገጠሚቸዉን የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዎች በየዓመቱ የማደስ፤
14. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ገጣሚ ድርጅቶች ያስመጡትን የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ አይ ኤም ኢ ( IMEI) ቁጥር እና መለያ ቁጥር ( SERIAL NUMBER) ወደ መተግበሪያዉ የማስገባት፤
15. ገጣሚ ድርጅቱ የመሳሪያዉ ስታንዳርድ ጥራት ለማረጋገጥ የሚወጣዉን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡
16. ገጣሚ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ያልወሰደ ቴክኒሽያን ወደ ሥራ ማሰማራት አይችልም፡፡
17. ገጣሚ ድርጅቱ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን፤ በመሳሪያዉ ዉስጥ ያለዉን ሲም ካርድ እና የተሞላዉን የሞባይል ዳታ ለባለንብረቱ በሽያጭ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡ ባለ ንብረቱ ለ3ኛ ወገን ሲያስተላልፍ ሲም ካርድ እና የተሞላዉን የሞባይል ዳታ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡
18. ገጣሚ ድርጅቱ አገልግሎቱን አቋርጦ ከዘርፉ በሚወጣበት ጊዜ በእጁ ላይ የሚገኙትን የተሽከርካሪ መረጃ ለአገልግሎቱ ማስረከብ እና ክሊራንስ መውሰድ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**16. ክልከላ**

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 በልዩ ሁኔታ ከተፈቀደላቸዉ ተሽከሪካሪዎች በስተቀር የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጥም በዚህ መመሪያ ላይ የተካተተ ማንኛዉም ተሽከሪካሪ መሳሪያዉን ሳይገጥም በመንገድ ላይ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነዉ፡፡
2. በዚህ መመሪያ መሠረት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጥም የተካተተ ተሽከሪካሪ ቋሚ የመለያ ቁጥር ሰሌዳ ማግኘት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር እና በተላላፊ ወይም በዕለት ሰሌዳ በልዩ ሁኔታ ተሽከሪካሪዉ ወደ ሥራ ከተሰማራ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን ሳይገጥም መንቀሳቀስ የለበትም፡፡

**17. ቅጣት**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው የዚህ መመሪያ አካል በሆነው ሠንጠረዥ "ሀ" መሰረት ቅጣት ይጣልበታል፡፡

**18. አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

አሽከሪካሪዉ ወይም የአሽከሪካሪዉ ባለቤት፡

1. በተሽከሪካሪዉ ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ያላስገጠመ እንደሆነ መሳሪያዉን እስኪያስገጥምና ስለመግጠሙ ህጋዊ መረጃ እስከሚያቀርብ ድረስ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ የአሽከሪካሪዉን የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በመያዝ ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት በማድረግ እንዲታገድ ያደርጋል፡፡
2. የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን በህጉ ከተፈቀደዉ የፍጥነት ወሰን በላይ የገጠመ ወይም አግባቢነት በሌለዉ ሁኔታ ያሸገ እንደሆነ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ተገቢዉን ማስተካከያ እስከሚያደርግ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለጊዜዉ ይዞት ሊያቆየዉ ይችላል፡፡

**19. የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ስነ- ስርዓት፡**

1. በዚህ መመሪያ አፈጻጸም ላይ ቅሬታ ያለዉ ማንኛዉም ሰዉ ቅሬታዉ ከተፈጠረ ቀን አንስቶ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ዉስጥ ጉዳዩ ለሚመለከተዉ የአገልግሎቱ ስራ ክፍል ወይም ለሚመለከተዉ የትራንስፖርት ቢሮ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታዉ የቀረበለት ክፍል ለቅሬታ አቅራቢዉ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ዉስጥ ምላሹን ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያደረበት ሰዉ ቅሬታዉን ለአገልግሎቱ ወይም ለሚመለከተዉ የትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ሀላፊ ማቅረብ ይችላል፤
4. የአገልገሎቱ ወይም የቢሮው የበላይ ሀላፊ በሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ ተቋማዊ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

16. **አባሪ ሰነድ**

ከዚህ መመሪያ አተገባበር ጋር በተያያዘ አገልግሎቱ የሚያወጣቸዉ መስፈርቶች እና የሚያስተላልፋቸዉ የደብዳቤ ልዉዉጦች የዚህ መመሪያ አባሪ ሰነዶች ይሆናሉ፡፡

19. የተሻሩ መመሪያዎች

የተሽከርካሪዎች የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ ስለመግጠም እና ስለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 692/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

**20. ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

**21. መመሪያዉን ስለማሻሻል**

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለዉ ይችላል፡፡

20. **መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ …… ቀን /2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ዶ/ር ዓለሙ ስሜ**

**የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚንስቴር ሚኒስትር**

ሠንጠረዥ ሀ

| ተ.ቁ | የጥፋቶች ዝርዝር | የገንዘብ ቅጣት መጠን |
|---|---|---|
| 1 | ማንኛዉም የተሽከሪካሪ ባለንብረት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ እንዲገጠም በመመሪያዉ የተካተተዉን ተሽከሪካሪ መሳሪያዉን ሳይገጥም እንዲሽከረከር የፈቀደ | 3000 ብር |
| 2 | ማንኛዉም የተሽከሪካሪ ባለንብረት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ ሲበላሽ እንዲስተካከል ያላደረገ | 2000 ብር |
| 3 | ማንኛዉም አሽከሪካሪ አገልግሎቱ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ እንዲገጠምለት በመመሪያዉ ላይ የተካተተዉ ተሽከሪካሪ ዓይነት የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን ሳይገጥምለት ያሽከረከረ | 1000 ብር |
| 4 | ማንኛዉም አሽከሪካሪ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ በተቀመጠዉ ስፔስፊኬሽን መሠረት የተገጠመና በታሰረዉ የፍጥነት ልክ (ጂ.ፒ.ኤስ) ጋር የተናበበ ወይም በአግባቡ | 1000 ብር |

| | | |
|---|---|---|
| | የተገጠመ፤የታሸገ እና በትክክል የሚሰራ መሆኑን ሳያረጋግጥ ያሽከረከረ | |
| 5 | ማንኛዉም አሽከሪካሪ በተሽከሪካሪዉ ላይ የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ መገጠሙን የሚያሳይ ሰርቲፊኬት ያልያዘ | 1000 ብር |

ሠንጠረዥ ለ

**<u>የተሸከሪካሪ ዓመታዊ ምርመራ እንዲያከናዉን ሥልጣን በተሰጠዉ አካል የሚፈፀሙ ጥፋቶች እና የሚያስከትሉት ቅጣት</u>**

| ተ.ቁ | የጥፋቶች ዝርዝር | የሚወሰድ እርምጃ |
|---|---|---|
| 1 | የተሽከሪካሪ ዓመታዊ ምርመራ እንዲያከናዉን ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ምርመራ ሳያደርግ ወይም የፍጥነት መገደቢያው ላልተገጠመለት ተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የሰጠ | በዓመታዊ የተሽከርካሪዎች ደህንነት የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አሰጣጥን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 668/2013 መሰረት ይቀጣል |

ሠንጠረዥ ሐ

**<u>የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ በሚያቀርቡ ድርጅቶች የሚፈፀሙ ጥፋቶች እና የሚያስከትሉት ቅጣት</u>**

| ተ.ቁ | የጥፋቶች ዝርዝር | የሚወሰድ እርምጃ |
|---|---|---|
| 1 | የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉ የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ የጠበቀ መሳሪያ ያልገጠመ ወይም በተሽከርካሪ ከፍተኛ የፍጥነት ወሰን ደንብ ቁጥር 492/2014 መሰረት የፍጥነት ወሰኑን ያላስተካከለ | ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂ |
| | | ለ2ኛ ጊዜ ለ3 ወር ፈቃዱ ይታገዳል |
| | | ለ3ኛ ጊዜ ፍቃዱ ይሰረዛል |
| 2 | ማንኛዉም የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የሚያቀርብ አገልግሎቱ በየጊዜዉ የሚያወጣቸዉን የአሠራር ሥርዓቶች ተግባራዊ ያላደረገ፤ | ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂ |
| | | ለ2ኛ ጊዜ ለ3 ወር ፈቃዱ ይታገዳል |
| | | ለ3ኛ ጊዜ ፍቃዱ ይሰረዛል |
| 2 | የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት የሌለው ቴክኒሽያን ወደ ሥራ ያሰማራ፡፡ | ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂ |
| | | ለ2ኛ ጊዜ ለ3 ወር ፈቃዱ ይታገዳል |

| | | |
|---|---|---|
| | | ለ3ኛ ጊዜ ፍቃዱ ይሰረዛል |
| 3 | ማንኛዉም የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የሚያቀርብ ገጣሚ ድርጅቱ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ ፍጥነት መገደቢያ መሳሪያዉን፤ በመሳሪያዉ ዉስጥ ያለዉን ሲም ካርድ እና የተሞላዉን የሞባይል ዳታ ለባለንብረቱ በሽያጭ ያላስተላለፈ፡፡ ባለ ንብረት ለ3ኛ ወገን ሲያስተላልፍ ሲም ካርድ እና የተሞላዉን የሞባይል ዳታ ያላስተላለፈ፡፡ | ለመጀመሪያ ጊዜ የፅሁፍ ማስጠንቀቂ |
| | | ለ2ኛ ጊዜ ለ3 ወር ፈቃዱ ይታገዳል |
| | | ለ3ኛ ጊዜ ፍቃዱ ይሰረዛል |